7ኛ ዓመት ቁጥር 8
7th Year No. 8

ባህር ዳር መጋቢት 21 ቀን 1994 ዓ.ም
Bahir Dar March 30,2002

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
የንዱ ዋጋ ብር 1.75
Unit price

ማውጫ	Contents
አዋጅ ቁጥር 64/1994 ዓ/ም የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ	Proclamation No. 64/2002 Proclamation for Establishing the Secretariat of the Amhara National Regional Council and for Defining its Powers and Duties No. 64/2002

አዋጅ ቁጥር 64/1994 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጽ/ቤትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ተሻሽሎ በተቀረፀው የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ አደረጃጀትና የሥልጣን አካላቱ ድልድል መርህ መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ከአስፈፃሚው አካል የአሠራር ተፅዕኖ ተላቆና ራሱን ችሎ እንዲዋቀርም ሆነ የራሱ ነፃ አመራር እንዲኖረው በተሻሻለው የ1994 ዓ.ም ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 50 እና 51 ድንጋጌዎች ስር የተወሰነ በመሆኑ፤

ከዚህም የተነሣ የክልሉ ም/ቤት በሕገ-መንግሥቱ የተጣለበትን ባለብዙ ፈርጅ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ሕገ-መንግሥታዊ ውሣኔ መሠረት ይህንኑ የራሱን ጽ/ቤት በሕግ መመሥረት፣ ማደራጀትና ሥልጣንና ተግባሩን መወሰን ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No.64/2002

Proclamation for Establishing the Secretariat of the Amhara National Regional Council and for Defining its Powers and Duties No.64/2002.

WHEREAS, in accordance with the revised principle of organizing the Amhara National Regional Government and distributing its power organs, it is provided under Provisions of Articles 50 and 51 of the 2001 revised Constitution that the Amhara National Regional Council shall organize itself and have autonomous leadership free from the operational pressure of the Executive body;

WHEREAS, it has therefore become necessary pursuant to the constitutional Provisions, to legally establish and organize the Secretariat of the Regional Council and Define its Powers and Duties so that the Council may efficiently discharge its multiple Constitutionally provided responsibilities;

ከዚህም በተጨማሪ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 75 /1/፣ 87 /1/ እና 99 /1/ ድንጋጌዎች መሠረት በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የብሔረሰብ፣ የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች የየራሳቸው ጽ/ቤቶች እንዲኖራቸውና በነፃነት እንዲመሩ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it has become necessary, in accordance with the provisions of Articles 75(1), 87 and 99(1) of the Constitution, to enable the Nationality, Woreda and Kebele Councils in the Region have their own independently run offices;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, in accordance with the powers vested in it under Article 49(3)(1) of the 2001 revised Constitution, the Amhara National Regional Council hereby issues this Proclamation:

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

PART ONE
General

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 64/1994ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Proclamation for Establishing the Secretariat of the Amhara National Regional council and for Defining its Powers and Duties No.64/2002. "

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. " የክልል ምክር ቤት" ማለት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ስር የተቋቋመውና ዝርዝር ሥልጣንና ተግባሩ የተገለፀው አካል ነው::
2. "አፈ-ጉባኤ " ማለት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ከክልሉ ም/ቤት አባላት መካከል ተመርጦ ለም/ቤቱ የሥራ ዘመን እንዲያገለግል የተሠየመ ባለሥልጣን ወይም የሕዝብ ባለአደራ ሲሆን እንደ አግባብነቱ የብሔረሰብ፣ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎችንም ይጨምራል::

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1. "Regional Council" means the body established and vested with powers and duties pursuant to Article 49 of the 2001 Revised Constitution of the National Region.
2. "Speaker" means an authority or public trustee elected from among the members of the Regional Council pursuant to Article 51(1) of the Constitution cited above to serve during a parliamentary term. Where relevant, this may also apply to the Speakers of nationality, Woreda and Kebele Councils.

ክፍል ሁለት

ስለክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አላማ አደረጃጀትና ተልዕኮ

3. ስለመቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ "ጽህፈት ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሠውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::
2. የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለአፈ-ጉባዔው ይሆናል::

4. ስለሌሎች የተዋረድ ጽ/ቤቶች ምስረታና አደረጃጀት

1. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብሔረሰብ፣ የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት የሚኖሯቸው የስራ ማከናወኛ ጽ/ቤቶች በዚህ አዋጅ ህጋዊ ሰውነት አግኝተው ተቋቁመዋል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከቱት የተዋረድ ም/ቤቶች ጽ/ቤቶች በዚህ አዋጅ ለክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት የተሠጠውን ዝርዝር ስልጣንና ሀላፊነት ለስራቸው በሚያስፈልጋቸው መጠን ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔረሰብ፣ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች ጽ/ቤቶች ወደፊት ራሳቸውን ችለው በበቂ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ እስኪደራጁ ድረስ በየደረጃው በአፈ-ጉባኤዎች እየተመሩ በትይዩ የሚገኙትን የአስተዳደር ጽ/ቤቶች ድጋፍ ሰጪ ኃይል ሊጠቀሙ ይችላሉ::

5. መደበኛ አድራሻ

የክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት መደበኛ አድራሻ ባህርዳር ሲሆን ሌሎች ም/ቤቶች በልዩ ሁኔታ ተለዋጭ ውሣኔ ካላደረጉ በስተቀር ጽ/ቤቶቻቸውን የሚያቋቁሙት በርዕሳነ ከተሞቻቸው ይሆናል::

PART TWO

Establishment, Accountability, Objectives and Mission of Secretariat

3. Establishment

1. The Secretariat of the Amhara National Regional Council, hereafter referred to as "secretariat", has been established by this Proclamation as an independent body with legal personality.
2. The Secretariat shall be accountable to the Speaker.

4. Establishment and Organization of other Hierarchical Offices of the Secretariat

1. Pursuant to Provisions of the Constitution working Offices of Nationality, Woreda and Kebele Councils in the National Region have been established with legal personality by this Proclamation.
2. The Hierarchical Offices under sub-article 1 above, may exercise the powers and responsibilities given to the Secretariat of the Council as much as their duties may necessitate them.
3. Without prejudice to Sub-article 1 of this Article, the Nationality, Woreda and Kebele Offices, until they organize themselves with necessary manpower and material resources, may make use of support forces of the parallel Administrative Offices, under the leadership of the Speakers at all levels.

5. Official Address

The Secretariat of the Regional Council shall have its seat in Bahir Dar while the other Council offices shall be seated in their respective capitals unless they make alternative decisions due to special circumstances.

6. አላማ

የክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት መሠረታዊ አላማ ም/ቤቱና አመራሩ በሕገ-መንግሥቱ የተጣለባቸውን ሕዝባዊ አደራና ሕጋዊ ኃላፊነት በብቃትና በታማኝነት እንዲወጡ ማስቻልና ተልኳቸውን ማሳካት ነው።

7. የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት በመሆን ያገለግላል፤
2. ለክልሉ ም/ቤትና ለልዩ ልዩ ኮሚቴዎቹ ሁለገብ የጽህፈት ስራ አገልግሎት ይሠጣል፤
3. ለክልሉ ም/ቤትና ኮሚቴዎቹ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ያሰናዳል፣ ያደራጃል፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን ያሟላል፤
4. የም/ቤቱና የኮሚቴዎቹ ቃለ ጉባዔዎች፣ ውሣኔዎችና ሌሎች ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበው እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
5. ለክልሉ ም/ቤት አካላትና ለአባላቱ የቤተ-መጻህፍት፣ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሠጣል፤
6. የክልሉ ም/ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸው አዋጆችና ደንቦች በቅርጽም ሆነ በይዘት በወቅቱ ተሟልተውና ተስተካክለው ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲተረጐሙ፣ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ እንዲታተሙና ለሚመለከታቸው አካላትም ሆነ ለተገልጋዩ ሕብረተሠብ እንዲሰራጩ ያደርጋል፤
7. በክልሉ ም/ቤት የሚወጡ ጋዜጦች፣ መጽሄቶችና በራሪ ጽሁፎች ዝግጅት ህትመትና ስርጭት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

6. Objectives

The basic objective of the Secretariat shall be to facilitate conditions of the Regional Council and its leadership to honestly and efficiently carry out the public trust and responsibilities reposed in them by the Constitution.

7. Powers and Duties of Secretariat

Pursuant to this Proclamation, the Amhara National Regional Council shall have the following powers and duties:

1. It shall serve as the Office of the Speaker of the Regional Council.
2. It shall provide all round secretarial services for the Regional Council and the various Committees.
3. It shall prepare and organize conference halls for the Regional council and Committees and satisfy meeting utilities.
4. It shall ensure that Committee minutes, resolutions and other documents are properly documented and preserved.
5. It shall provide library, research and information service for organs and members of the Regional Council.
6. It shall cause all Proclamations and Regulations occasionally issued by the Regional council, translated into English, complete and emended both in form and content on time; printed in the Regional Zikere Hig Gazette and distributed to concerned bodies and the public.
7. It shall follow up and oversee the preparation, printing and distribution processes of newspapers, magazines and leaflets published by the Regional Council.

8. ከአፈ-ጉባኤው በሚሰጠው አመራር መሠረት የም/ቤቱን አባላትና ተጋባዥ እንግዶች ይቀበላል፣ተፈላጊው የመስተንግዶ አገልግሎት ተሟልቶ የቀረበላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

9. የክልሉን ም/ቤት ጨምሮ የየደረጃው ም/ቤቶች አቅም የሚጐለብትበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ይደግፋል፣

10. ምክር ቤቱ ያሳለፋቸው ውሣኔዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፣

11. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

12. የክልሉን ም/ቤት ሥራ ለማሳካት የሚረዱና በአፈ-ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

8. <u>ስለጽ/ቤቱ አደረጃጀት፣ አመራርና ተጠሪነት</u>

1. ጽ/ቤቱ አፈ-ጉባኤውንና ም/አፈ-ጉባኤውን በሞያ አገልግሎት የሚያግዙና በአፈ-ጉባኤው የሚሾሙ አማካሪዎችን ጭምር የያዘ ሲሆን ይህንኑ በማካተት አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ በአፈ-ጉባዔው አማካኝነት ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያስወስናል፣

2. ጽ/ቤቱ በአፈ-ጉባዔው አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት በሚሾም አንድ የበላይ ኃላፊ ይመራል፣ ይተዳደራል፣

3. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነት ለአፈ-ጉባዔው ይሆናል።

9. <u>የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

8. It shall, under the instruction of the Speaker, receive Council members and invited guests and see that ample hospitality services are available.

9. It shall ensure and help create conducive conditions for developing the capacity of Hierarchical Council Offices including the Secretariat of Regional Council.

10. It shall cause the decisions passed by the Regional Council reach the concerned bodies on time.

11. It shall own properties, enter into contracts, sue and be sued.

12. It shall carry out activities that help the work of the Regional Council succeed and other related duties given by the Speaker.

8. **<u>Organization, Leadership and Accountability of Secretariat</u>**

1. The Secretariat shall have a staff comprising the Speaker, Deputy Speaker including advisors to be appointed by speaker to give professional services and through the Speaker it shall, study and submit organizational structure necessary to achieve its goals to the Regional council and have it approved.

2. The Secretariat shall be led and administered by a head appointed by the Regional Council upon the recommendation of the Speaker.

3. The Head of the Secretariat shall be accountable to the Speaker.

9. **<u>Powers and Duties of the Head of the Secretariat</u>**

The Head of the Secretariat shall have the following powers and Duties:

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር ለጽህፈት ቤቱ የተሠጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣
2. ከአፈ-ጉባዔው በሚሠጠው አመራር መሠረት የጽህፈት ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
3. የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሕጐችና ደንቦች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
4. የጽህፈት ቤቱን አመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባዔው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
5. የጽህፈት ቤቱን ሂሣብ ያንቀሳቅሳል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት የፋይናንስ ሕግን መሠረት አድርጐ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
6. ከአፈ-ጉባዔው በሚሰጠው አመራር መሠረት ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፣
7. የጽህፈት ቤቱን እንቅስቃሴና የሂሣብ ሪፖርት ለአፈ-ጉባዔው ያቀርባል፣
8. በአፈ-ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣
9. ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል ከተግባርና ሀላፊነቱ ከፊሉን በውክልና ለጽ/ቤቱ የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. በጀት

የጽህፈት ቤቱ በጀት በክልሉ ም/ቤት ይመደባል፡፡

1. He shall implement the Powers and Duties given to the Secretariat under article 7 of this Proclamation.
2. He shall oversee, direct, co-ordinate and control the functions of the Secretariat in accordance with the directives of the Speaker.
3. He shall employ and manage the personnel of the Secretariat in accordance with the civil service rules and regulations.
4. He shall prepare and submit the Secretariat's annual budget and projects to the Speaker and execute same when approved.
5. He shall deal with the Secretariat's account and disburse money based on the approved budget and financial regulations.
6. He shall, under the speaker's instructions, represent the Secretariat in all contacts made with third parties.
7. Prepare a report on the activities and financial accounts of the Secretariat and submit same to the Speaker.
8. Carry out such other functions as given to him by the Speaker.
9. He may, in the interests of efficiency, share out some of his powers and responsibilities between lower officials and staff members.

PART THREE

Miscellaneous Provisions

10. Budget

The budget of the Secretariat shall be allocated by the Regional Council.

11. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣
2. የጽህፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር አማካኝነት ይመረመራሉ::

12. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በተዋረድ ም/ቤቶች ጽ/ቤቶች ኃላፊነትና አሠራር ላይ እንዳስፈላጊነቱ ተፈፃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

13. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የክልሉ ም/ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል::

14. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

አፈጉባኤው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

15. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 21 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
መጋቢት 21 ቀን 1994 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

11. <u>Books of Accounts</u>

1. The Secretariat shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The books of accounts and documents of the Secretariat shall be audited by the Auditor General of the Region.

12. <u>Scope of Applicability</u>

The relevant Provisions of this Proclamation may be applicable to the responsibilities and operations of the hierarchical councils' offices as deemed necessary.

13. <u>Powers to issue Regulations</u>

The Regional Council may necessary for the implementation of this proclamation.

14. <u>Issuance of Directives</u>

The Speaker may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

15. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force as of the 30th day of March, 2002.

Done at Bahir Dar,
this 30th day of March, 2002

Yosef Retta
President of the Amhara
National Region